# የአብክመ ፍትሕ ቢሮ

## የ2019 በጀት ዓመት የአሻጋሪና ዘላቂ ልማት ዕቅድ

ሰኔ 2018 ዓ.ም

ባህርዳር፤

# ማውጫ


መግቢያ ........ 3
1. የፍትህ ቢሮ ቁልፍ ሚና ........ 4
2. የሁኔታ ትንተና ........ 6
2.1. ክልላዊ የሁኔታ ትንተና ........ 6
2.2. የፍትህ ቢሮ ተቋማዊ ዳሰሳ ሁኔታ ........ 9
3. ርዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች ........ 18
4. ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች፣ የትኩረት መስኮች፣ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ........ 19
4.1. ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ........ 19
4.2. የትኩረት መስክ ........ 19
4.3. የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 21
5. ዓላማ፣ ስትራቴጂክ ግቦች እና ተግባራት ........ 21
5.1. ዓላማ ........ 21
5.2. ዋና ዋና ግቦች /strategic Objectives/ ........ 21
5.3. የ2019 በጀት ዓመት ግቦች ........ 22
6. የማስፈጸሚያ ስልቶች፣ የማስፈፀሚያ ሀብት/በጀት/ ........ 30
6.1.የማስፈጸሚያ ስልቶች፣ ........ 30
6.2.የማስፈፀሚያ ሀብት/በጀት/ ........ 31
7. መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶች ........ 32
8. የክትትልና የግምገማ ስርዓት ........ 36
9. የድርጊት መርሃ ግብር ........ 37

**መግቢያ**

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በ25 አመቱ የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ አና በ5 አመቱ ስትራቴጅክ እቅዱ ላይ የክልሉን ሠላምና ደህንነት እንዲሁም የህግ የበላይነት ማረጋገጥ አንዱ ስትራቴጅክ ምሰሶ አድርጎ በመያዝ የክልሉን ሠላምና ደህንነት እንዱሁም የህግ የበላይነት በማረጋገጥ ችግርን በውይይት የመፍታት ልምምዱን ማሳደግ፣ የክልሉን የመደራደር አቅም ማጎልበት፣የሽግግር ፍትህን መተግበርና ክልሉ ሚናውን በሚጠበቅበት ደረጃ እንዲወጣ ማድረግ፣ ሀገራዊ ምክክርን ማጠናከር፣ የፍትህ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነታቸውን በሚገባ እንድወጡ ማስቻል፣ የክልሉ ነዋሪዎች በክልሉ መንግስት ላይ ያላቸው አመኔታ እንዲጨምር ማድረግ ከፍትህ ተቋማት የሚጠበቅ ተግባር እንደሚሆን አሰቀምጧል፡፡

የአብክመ ፍትህ ቢሮም አንዱ የክልሉ የፍትህ ተቋም በመሆን በክልሉ ህግ አውጪ አካላት በተደነገጉ አዋጆች እና ደንቦች መሰረት ተቋቁሞ በክልሉ ውስጥ የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ፣ ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን፣ የዜጎች ሰብአዊ ዴሞክራሲዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር፣ የኢፌዴሪ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ፖሊሲ በክልሉ መተግበሩን የማረጋገጥ፣ የክልሉ መንግስት የህግ አማካሪ በመሆን፤ በክልሉ የሚወጡ ህግጋት ከህገ-መንግስቱና ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውንና የወጡ ህግጋት ተፈፃሚነት ማረጋገጥ እንዲሁም የብሄራዊ ክልሉን መንግስትና ሕዝብ መብትና ጥቅም ማስጠበቅ ተልዕኮ ተሰጥቶታል፡፡

ቢሮው ይህንን ተልእኮ ለመወጣት በ2018 በጀት አመት ከክልሉ መንግስት የ25 አመት የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታና ከ5 አመቱ ስትራተጅክ እቅድ እንደሁም ከ5 አመቱ የፍትህና የዳኝነት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የተቀዳ አመታዊ እቅድ በማቀድ ሲተገብር ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም እንደ ሀገር የተዘጋጀውን የፍትህ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ በማድረግ የ2018 በጀት አመት የፍትህ ትራንስፎርሜሽን እድቅ በማቀድ ተግባራዊ በማድረግ በርካታ ውጤቶችን አስመዝግቧል፡፡

በፍትህ ዘርፉ የነበሩትን ህግጋት የማሻሻልና አዳዲስ ህግጋትን እንዲወጡ በማድረግ በርካታ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

ይሁን እንጅ የፍትህ ዘርፉ ሕዝብና መንግስት የሚጠብቁትን ውጤት ከማስመዝገብ አኳያ አሁንም በርካታ ችግሮች አሉበት፡፡ በክልላችን የተፈጠረው አለመረጋጋት በፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ በእቅድ አፈፃፀም ግምገማዎች፣ ከባለድርሻና አጋር አካላት እንዲሁም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር

በተካሄዱ የምክክር መድረኮች በክልሉ ዉስጥ የህግ የበላይነት እንዲከበርና ሰላምና መረጋጋት እንዲመጣ፤ እንዲሁም የመንግስት በአገልግሎት አሰጣጥ እንድሻሻል ቅሬታዎች ቀርበዋል፡፡

ከላይ ከተገለፁት ስኬቶችና ተግዳሮቶች መነሻ በማድረግ በ2018 በጀት አመት ዕቅድ አፈጻጸም የተመዘገቡ ለውጦችን በማጠናከርና የታዩ ክፍተቶችን በመቅረፍ በክልሉ ዉስጥ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ፤ ሰላምና ደህንነትን ለማስፈን እና የፍትህ አገልግሎት አሰጣጣችንን ቀልጣፋና ዉጤታማ ለማድረግ ከ25 ዓመቱ የአሻጋሪ ዕድገትና ዘላቂ ልማት ዕቅድ፣ ከ5 ዓመቱ ስትራቴጅክ እቅድ፤ ከዳኝነትና የፍትህ ዘርፍ እንዲሁም ከቢሮው የ5 ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የተቀረሰና በእቅዶቹ የተለዩ የትኩረት መስኮች፣ የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂክ ግቦች መነሻ በማድረግ ይህ የ2019 በጀት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1. የፍትህ ቢሮ ቁልፍ ሚና

በሕዝብ አስተዳደር የመንግስት ሥርዓት የሕግ የበላይነትን በማስከበር ሰላምና ደህንነትን ማስፈን የመንግስት ተቀዳሚ ኃላፊነት ነው፡፡ የሕግ የበላይነት፣ሰላምና ደህንነት፣ሁለንተናዊ ልማትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን በማፋጠን ድህነትንና ኋላቀርነትን በመቀነስ የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ የሕግ የበላይነት ባልሰፈነበት፣ ሰላምና ደህንነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የመንግስት ቅቡልነት መሸርሸሩ እና ሥርዓት አልበኝነት መንሰራፋቱ አይቀሬ ነው፡፡ ሙስናን በመከላከል እና የአስተዳደር ፍትሕን በማስፈን ረገድ የፍትሕ ዘርፉን በሚፈለገው ልክ ጠንካራ ቁመና እንዲኖረው ማድረግ ካልተቻለ በክልሉ ውስጥ የሚፈለገውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እና ሁለንተናዊ ልማት ማሳካት አይቻልም፡፡

መንግስት ሕግ ከማስከበር፣ ሰላምና ደህንነትን ከማስፈን ባሻገር በአገር ሁለንተናዊ ልማትና እድገት የሚጫወተው ሚና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ በመሄዱ የፍትሕ ተቋማት ኃላፊነት በዚያው መጠን ከወትሮው በተለዬ መልኩ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በተለይም በታዳጊ አገራት የመንግስታት ሚና ጎላ ብሎ የሚታይ ሲሆን መንግስታት የገበያ ክፍተትን ለመሙላት በኢኮኖሚው ውስጥ ሃብት የሚያስተዳድሩበት ሁኔታ እያደገ እና እየሰፋ መጥቷል፡፡ መንግስታት ከተለመደው መንግስታዊ ተግባራት በተጨማሪ አዳዲስ ኢኮኖሚ ነክ ሚናዎችን እየተወጡ መምጣታቸውን ተከትሎ የፍትሕ ተቋማት ኃላፊነት ከወትሮው በተለዬ መልኩ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በአጠቃላይ የፍትሕ ተቋማት ሰላምና ደህንነትን በማረጋገጥ፤ የህግ የበላይነትን በማስከበር ለልማት ምቹ ሁኔታ በማደላደል እና ሁለንተናዊ እድገት በማፋጠን ረገድ አይተኬ ሚና አላቸው፡፡ በመሆኑም ልማትና እድገትን ለማረጋገጥ የሚታሰብ ማንኛውም

እቅድ የፍትሕ ዘርፍ ተግባራትን ማጠንጠኛ ማዕከል ማድረግ እና የዘርፉን ሚና ብቻ ታሳቢ አድርጎ ከመቁጠር ባሻገር በየዕለት ከዕለት ጥረት ውስጥ ጎልቶ እንዲታይ ለማድረግ የሚለኩ ግቦችና ተግባራት ተቀምጠውለት ክትትል፣ ግምገማ እና ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል።

ከዚህ አኳያ የክልሉ ፍትሕ ቢሮ ዋነኛ የሕግ አስከባሪ ተቋም (Chief Law Enforcement Office)፣ የፖሊሲና ሕግ አማካሪ እና ሕግ አርቃቂ በመሆኑ በክልሉ የሚወጡ ሕግጋትን በጥናት ላይ የተመሰረቱ፣ ፍትሐዊ፣ ተገማችና ጥራት ያላቸው እንዲሆኑ እና ሰዎች በመንግስት አሰራር ላይ ሙሉ እምነት እንዲኖራቸው በማድረግ የንግድና ኢንቨስትመንት ስራቸውን ያለ ምንም ስጋትና መጠራጠር እንዲከውኑ፤ የኢንቨስትመንት ስራ እና የአካባቢ ጥበቃን የሚመለከቱ ህግጋት የዛሬውን እና የቀጣዩን ትውልድ ፍላጎቶች ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ የሚመለከቱ እና ዘላቂ ልማትን ታሳቢ ያደረጉ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ቢሮው ሕግጋትን ከማርቀቅ ባሻገር በክልሉ መንግስት የሚወጡ ሕግጋትን ተፈጻሚነታቸውን በመከታተል፣ የሕግ አስፈጻሚው አካል ተግባሩን በሕግ በተሰጠው የሥልጣን ገደብ ልክ እየተገበረ መሆን አለመሆኑን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የመንግስት አሰራር ግለጽነትና ተጠያቂነት የተላበሰ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል።

የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውንና የወንጀል መከላከል እስትራቴጅውን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን የመስራት፣ የማስተባበር፣ የመከታተል እና የማረጋገጥ ተግባራትን ይፈጽማል። የወንጀል ፍትሕ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀት፣ ለመተንተንና ለማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት የወንጀል መከላከል ስትራቴጂና ስልት በመንደፍ ወንጀልን ይከላከላል፤ምርመራን በበላይነት ይመራል፣ ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ፈጻሚዎችን ወደ ሕግ የማቅረብ፣ ጥራት ያለው ክስ በማዘጋጀት እና በፍትሕ አደባባይ ብቃት ያለው ክርክር በማቅረብ የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል።

በፍትሐብሄር ፍትህ አስተዳደር ዘርፍ የክልሉን መንግስትና ህዝብ መብትና ጥቅም ሕጋዊ ወኪል በመሆን በፍርድ ቤት እና ከፍርድ ቤት ውጭ ባሉ አማራጭ መንገዶች እንዲከበሩ፣ ያለአግባብ እንዳይባክን እና እንዳይመዘበር ተገቢውን ክትትል ና ቁጥጥር ያደርጋል፤ልዩ የህግ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ነፃ የህግ ድጋፍ በመስጠት ሰዎች ያለ ፍርሃትና ስጋት ኑሯቸውን እንዲመሩ፣ ለንብረት መብት ዋስትናና ጥበቃ በመስጠት የተረጋጋ

ማኀበራዊ ግንኙነት እንዲሰፍን፣ ሕግ የማስከበር ባህል እንዲዳብር እና ስር- እንዲሰድ በማድረግ በክልሉ ልማትና እድገት ላይ ቀጥተኛና አይነተና ሚና አለው፡፡

የሕግ አገልግሎት ዘርፍን በበላይነት በመምራት ረገድ ከጠበቆች ማህበርና ከሚመለከታቸው ሌሎች ተቋማት ጋር በጋራ በመሆን የጥብቅና አገለግሎቱን የመምራት፣ ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጡን የማስተባበር እና የክልሉን ተቋማት የህግ አገልግሎት የስራ ክፍሎችን አቅም የማሳደግና አፈጻጸማቸውን የመከታተል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ቢሮው የፍትህ ተደራሽነትን በማረጋገጥ፣ የመንግስትና የሕዝብን ጥቅሞች በማስጠበቅ እና ውስን የክልሉን ሃብትና ንብረት ከምዝበራና ከብክነት በመከላከል ረገድ በክልሉ ዕድገት ላይ ከፍተኛ አስተዎጾ አለው፡፡

በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ በየደረጃው በሚገኙ ዐቃብያነ-ህግ የሚሰጡ ውሳኔዎች ሙያዊ ነጻነትንና የተጠያቂነት ስርዓቱን የተከተሉ ስለመሆናቸው እና ዐቃቤያነህግ የሚያሳልፏቸው ውሳኔዎች የህዝብና መንስትን መብትና ጥቅም የሚያስከብሩ፣ወጥ፣ተገማች እና የህግ መሰረት ያላቸው ስለመሆናቸው የማረጋገጥና ህጋዊነት የጎደላቸው ውሳኔዎች የሚታረሙበት ስርአት የመዘርጋት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

የማረሚያ ቤት አስተዳደር ኮሚሽንን በመደገፍና በማጠናከር በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎችን ሰብዓዊ ክብር በጠበቀ ሁኔታ በማረምና በማነጽ ህግ አክባሪ እንዲሆኑ ማድረግ፤ የታረሙ እና የታነጹ ሰዎችን ወደ ማህበራዊ ህይወታቸው የመመለስ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ማድረግ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ኮሚሽኑ ታራሚዎች ከደጋጋሚ ወንጀል ፈጻሚነት እንዲርቁ፣ ወንጀል ጠል ና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ በማድረግ የሕግ የበላይትን ከማረጋገጥ ጎን ለጎን ለክልሉ የሰላም ግንባታ እና የልማት ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

## 2. የሁኔታ ትንተና

### 2.1. ክልላዊ የሁኔታ ትንተና

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ከሚገኙ አሥራ ሁለት ክልሎች አንዱ ነው፡፡ ክልሉ በኢትዮጵያ ሰሜን ምዕራብ እና ሰሜን ማዕከላዊ ክፍል ይገኛል፡፡ የክልሉ ዋና ከተማ የሆነችው ባህር ዳር ከዋና ከተማዋ አዲስ አበባ 565 ኪ.ሜ በደብረ ማርቆስ መስመር እንዲሁም 496 ኪ.ሜ በሞጣ መስመር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

በ8°41'4"-14°26'10" በሰሜን ኬክሮስ እና 35°26'50"-40°25'20" ምስራቅ ኬንትሮስ ውስጥ ይገኛል፡፡

አማራ በሰሜን ከትግራይ ክልል እና ኤርትራ፣ በምስራቅ ከአፋር ክልል፣ በደቡብ ከኦሮሚያ ክልል፣ በምዕራብ ከቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል እና ከሱዳን ጋር ይዋሰናል፡፡ ክልሉ ከሱዳን እና ኤርትራ (616.91 ኪ.ሜ) በሰሜን ምዕራብ እና በሰሜን አለም አቀፍ ድንበር አለው፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አጠቃላይ የቆዳ ስፋቱ 181,190.16 ካሬ ኪሎ ሜትር ወይም 18.12 ሚሊዮን ሄክታር አካባቢ ይሸፍናል፡፡ ይህ የቆዳ ስፋት የኢትዮጵያን አጠቃላይ የመሬት ስፋት 16 በመቶ ያህሉን የሚይዝ ሲሆን፣ ይህም ክልሉን ከኦሮሚያ እና ከሶማሌ ክልሎች ቀጥሎ በቆዳ ስፋት በሀገሪቱ ሦስተኛው ትልቅ ክልል ያደርገዋል፡፡

ክልሉ ለአስተዳደር ዓላማ በ14 አስተዳደር ዞኖች፣ 8 የሪጅዮ-ፖሊታን ከተሞች፣ 153 ገጠር ወረዳዎች እና 77 መካከለኛ እና አነስተኛ ከተማ አስተዳደሮች ተከፋፍሏል፡፡ በተጨማሪም ክልሉ በ3,544 የገጠር ቀበሌዎች እና 632 የከተማ ቀበሌዎች አሉት፡፡

ክልሉ የሃገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች የሚገኝበት ከመሆኑም በላይ ሁሉም የአየር ንብረት ዞኖች የሚገኙበት ነው፡፡ ከፍተኛ ቦታዎች በጮቄ፣ ጉና፣ ሰሜንተራሮች፣ ሰሜንና መሃል ወሎ አካባቢዎች ሲገኙ በጣም ዝቅተኛ ቦታዎች ደግሞ በሰሜን ምዕራብ ማለትም ቋራ፣መተማ እና ሁመራ አካባቢዎች ይገኛሉ፡፡ ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታ ከ479-4538 ሜትር የሚደርስ ሲሆን ክልሉም በተለምዶ አጠራር ስድሰቱን ዓይነት የአየር ንብረት ዞኖች በውስጡ የያዘ ሲሆን እነሱም ቁር፣ ውርጭ፣ ደጋ፣ ወይና ደጋ፣ ቆላ እና በረሀ አየር ንብረት ናቸው፡፡ ይህ ክልሉ ከያዘው የመሬት መጠን ውስጥ በረሀ 0.02፣ ቆላ 35.33፣ ወይና ደጋ 40.68፣ ደጋ 21.31፣ ውርጭ 2.28 እና ቁር 0.37 በመቶ ይሸፍናሉ፡፡

ከአብክመ ፕላንና ልማት ቢሮ በተገኘ መረጃ እና በ2019 ትንበያ መረጃ መሰረት  የአማራ ክልል ጠቅላላ ህዝብ ብዛት ወንድ 12,467,000 ሴት 12,585,199 ድምር 25,052,198 ነው፡፡ ከዚህም ህዝብ ውስጥ ህጻናት 9,842,283፣ አረጋውያን 2,964,382፣ አካል ጉዳተኞች 4,258,874 እንደሚሆኑ ይገመታል፡፡ እንዲሁም ወጣቶች 1,144,311 እንደሆኑ መረጃው ያሳያል፡፡ ከጠቅላላው ህዝብም ሴቶች 12,585,199 (50.24%) ድርሻ አላቸው፡፡ ስለሆነም ሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ በመሆናቸው ትኩረት ሰጥቶ መስራት የሚጠበቅ ሲሆን በተለይም የህፃናትን ጉዳይ

በትኩረት ይዞ መስራት ለነገ ሀገር ተረካቢ ዜጋ ለማፍራት ዓይነተኛ ሚና ይኖረዋል። ወጣት የህብረተሰብ ክፍሎችም የክልሉን የኢኮኖሚ ዘርፍ ለማሳደግና አምራች ኃይል በመሆኑ ለወንጀል እና የተለያዩ አጉል ሱሶች ተጋላጭ በመሆኑ በተግባራቶቻችን ውስጥ በማካተት ተገቢውን የህግ ድጋፍ እና ግንዛቤ መፍጠር ይገባል። ሴቶች የጠቅላላ ክልሉ ህዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ህዝብ የሚወክሉ በመሆኑና የሴቶች ተሳትፎ ለፍትህ ስርዓቱ ውጤታማነት ድርሻቸው የጎላ በመሆኑ የህግ ግንዛቤአቸውን በማሳደግ ለፍትህ ስርዓቱ መጠናከር እና ለመብቶቻቸው መከበር የድርሻቸውን እንዲወጡ ማስቻል ይገባል።

በአጠቃላይ የህዝብ ቁጥር የሚመጥን አገልግሎት ለመስጠት ቢሮአችን ልዩ ልዩ ስልቶችን በመጠቀም ለህብረተሰቡ የህግ ግንዛቤ ፈጠራ ስራ በመስራት የክልሉ ህዝብ ለፍትህ ስርኣቱ እና ለህግ የበላይነት መከበር የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲወጣ ማድረግ የሚጠበቅብን ሲሆን በወንጀል ፍትህ አስተዳደርና በፍትሐብሄር ፍትህ አስተዳደር ህብረተሰቡ የሚጠብቀውን አገልግሎት ለመስጠት ስራዎችን መስራት ይጠይቃል። በተለይም ከህብረተሰቡ የሚመጡ አቤቱታዎችን ተቀብሎ በቅልጥፋና ማስተናገድ፣ ከሰነድ አገልግሎት ጋር የተያያዙ ስራዎችን በቅልጥፍና መፈፀም እንዲሁም የመሶብ አገልግሎትን ተደራሽነትን በማስፋት ለህብረተሰቡ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ይገባል።

ክልሉ ካለፉት አምስት ዓመታት ጀምሮ በከፋ የግጭት እና ጦርነት ቀጠና ውስጥ በመቆየቱ በሁለንተናዊ መልኩ ማደግ እንዳይችል አድርጎታል። በተለይም በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ ቁሳዊ ውድመት፣ ስነ-ልቦናዊ ቀውስ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ እና አሁንም በክልሉ ውስጥ የተቀሰቀሰው ግጭት የክልሉን ህዝብ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በእጅጉ እየጎዳው እንደሚገኝና ዜጎች ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ እና ተቋማት በተሟላ መልኩ አገልግሎት መስጠት እንዳይችሉ እያደረገ ይገኛል። ከዚህ አኳያ እንደ ክልል የሚጠቀሱ ችግሮች ሽብርተኝነትና አክራሪነት፣ ያልተፈቱ የማንነትና የወሰን ጥያቄዎች፣ በከተሞች አካባቢ ህገ-ወጥ የመሬት ወረራ፣ በግጦሽ መሬት አጠቃቀምና ከወል መሬቶች ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ግጭቶች መኖር፣ የቅድመ ወንጀል መከላከል አፈፃፀም ደካማ መሆን፣ እንዲሁም ህገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ስርጭትና ዝውውር መጨመሩ፣ የሰው መግደል ወንጀል መጨመሩ፣ ህገ ወጥና ኮንትሮባንድ መባባሱ የሚሉት ዋና ዋና ችግሮች ናቸው።

በሌላ በኩል በክልል በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ምክንያት በክልሉ ውስጥ የፍትህን ተደራሽነት አለማረጋገጥ፣ የተከሳሽና ምስክር አለመቅረብና በዚህ ምክንያት አጥፊዎችን በወንጀል አለመጠየቅ፣ የመንግስትና ህዝብ ፍትሐብሄራዊ ጥቅሞችን በውጤታማነት አለመከላከልና

ማስመለስ አለመቻል፣ በሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አረጋዊያንና አካል ጉዳተኛ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች መባባስ ታይተዋል፡፡

ሌላው መሰረታዊ ችግር የዘርፉን ተቋማት ተግባር እና ኃላፊነት ከሚቋቋሙበት ወይም ከሚደራጁበት መሰረታዊ ዓላማ እና ከአለምአቀፍ ተሞክሮዎችና መርሆዎች አንጻር በሕግ በአግባቡ መለየት አለመቻል እና ሙያዊ የሆኑ ተቋማትን ገንብቶ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የፍትሕ አገልግሎት መስጠት አለመቻል ሲሆን ውጤታማነታቸውን ከፍ ለማድረግ የተቋማቱን አደረጃጀት ማጠናከር እና ተከታታይነት ያለው የአቅም ግንባታ ስራ መስራትን ይጠይቃል፡፡

ሳይንሳዊ የጥናትና ምርምር ሀሳቦችን በማፍለቅ ጠቋሚ ምክረ ሀሳብ ያፈልቃሉ ተብለው የተቋቋሙት የዘርፉ የስልጠናና የምርምር ተቋማትም በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ናቸው፡፡ የዘርፉን ተቋማት የፍትሕ አገልግሎት በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን የታገዘ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ችግር ይስተዋላል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በክልላዊ ሁኔታው የተመላከቱት ችግሮች ቢኖሩም በበርካታ አካባቢዎች አንፃራዊ ሰላም መፈጠሩና የህግ ማስከበር ተግባር እየተጠናከረ መምጣቱ፣ እንደሃገር የተጀመረውን የሀገራዊ ምክክር መድረክ መሰረት በማድረግ የክልሉ ህዝብ አጀንዳዎች ተለይተው ለብሄራዊ ምክክር ኮሚሽን መላክ መቻሉ፣ 7ኛው ሀገራዊ ምርጫ በክልላችን መካሄዱ፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረፀው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በክልሉ ለማስረፅ የስልጠና ሰነድ በማዘጋጀት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ መጀመሩ፣ የፍትህ አገልግሎቱን በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ በክልሉ አስቻይ ሁኔታ እየተፈጠረ መምጣቱ አመላካች ነው፡፡

በመሆኑም የክልሉን ሰላምና ደህንነት እና የህግ የበላይነትን፤ ዜጎችን ሰብአዊ መብቶች የሚያስከብሩ፤ የመንግስትና የህዝብ ጥቅሞችን ማስጠበቅ የሚችሉና ህገ ወጥነትን በመከላከል ህጋዊነትን የሚያረጋግጡ ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግና በየደረጃው የሚከሰቱ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን በሰለጠነ መንገድ በውይይትና በምክክር የመፍታት ልምድ ለማዳበር የሚያስችሉ ተግባራት በተከታታይ በመሰራታቸው አንፃራዊ መሻሻል እየታየ ይገኛል፡፡

## 2.2. የፍትህ ቢሮ ተቋማዊ ዳሰሳ ሁኔታ

የፍትህ ቢሮ ያለፈውን ዓመት አፈጻጸም የሁኔታ ትንተና ከፍትህ ትራንስፎርሜሽን ስራዎች አተገባበር፣ የሽግግር ፍትህ፣ አስተዳደራዊ ፍትህ፣ ተቋማዊ የመፈጸም አቅም፣ ተቋማዊና ሙያዊ ነፃነት እና ገለልተኝነትን ከማረጋገጥ አኳያ፣ ከአገልግሎት አሰጣጥ፣ ቅልጥፍና እና ጥራት፣ ከቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም፣ ከህብረተሰቡ የህግ ግንዛቤና

ተሳትፎ ማሳደግ፣ ከፍትህ ተደራሽነት እና ከፍትህ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር አኳያ ተዳሷል፡፡

## 1. የትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈጻጸም ያለበት ሁኔታ፤

በፍትህ ዘርፉ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲካሄዱ በነበሩ የማሻሻያ ስራዎች የተገኙ ውጤቶችና ስኬቶችን እንዲሁም የሚታዩ ክፍተቶች እንደመነሻ በመውሰድ በዘርፉ ላይ የሚፈለገው ለውጥ ሊመጣ የሚችለው ተጨባጭና ስር ነቀል ትራንስፎርሜሽናል መፍትሄዎች በመውሰድ መሆኑ በመታመኑ በፍትህ ዘርፉና በተቋም ደረጃ የፍትህ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2016-2018) ታቅዶ ሲተገበር ቆይቷል፡፡ በትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ 11 አምዶች የተቀረፁ ሲሆን የእያንዳንዱ ግብ ስኬት ከተቋሙ ተግባራት ጋር ተሳስሮ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በለውጡ የተመዘገቡ ውጤቶችንና በቀጣይ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች በጥቅል ለማመላከት ያህል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ከትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አላማዎች ዋነኛው የዘርፉን ተቋማት አደረጃጀትና አሰራር እንዲሁም የሰው ሀይልና የቴክኖሎጂ አቅም ዘመኑ በሚጠይቀው ደረጃ በማሻሻል ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ተልዕኮ በአግባቡ የሚወጡ ጠንካራ ተቋም ማድረግ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የቢሮውን አደረጃጀትና አሰራር በማሻሻል ክፍተቶችን የመሙላት፣ የአገልግሎት ቅልጥፍና ጥራትና ውቴታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ አሰራር ስርዓቶችና ህግ ማዕቀፎችን የማዘጋጀት ስራዎች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው ተሰርተዋል፡፡ ይኸውም፡- የመሰረተ-ማህበረሰብ የፍትህ አገልግሎትን ለማጠናከር ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን የማሰልጠን ስራ ተሰርቷል፤ በየደረጃዉ የሚገኙ የፍትህ ተቋማት አመራሮችን መልሶ የማደራጀት ስራወች ተሰርተዋል፤ የወንጀል፣ የአስተዳደርና ፍትሐብሔር ፍትህ ሥርዓት ፕሮግራም በአዲስ አስተሳሰብ በመምራት በወንጀል የተመዘበረን ገንዘብ የማስመለስ፤ የወንጀል የገንዘብ ቅጣትን የማስፈጸም፤ ለወንጀል ምስክሮች ጥበቃ የማድረግ እና ውዝፍ መዛግብትን የማጥራት ስራዎች በስፋት ተሰርተዋል፡፡ የተጠናከረ የንቃተ ህግ ትምህርትና ህግ ድጋፍ ማድረግን ተመለከተም የንቃተ ህግ ትምህርት፤ የህግ ምክር አገልግሎትና ነጻ የህግ አገልግሎት በስፋት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡
የሰው ሀይሉን አቅም ከማሳደግና ከማጥራት አኳያ በክልሉ ያጋጠመው የፀጥታ ችግር በተሟላ መንገድ ለመፈፀም ተግዳሮት ቢያጋጥምም በፍትህ ቢሮ ረጅም ጊዜ ያገለገሉ ሰራተኞች የማበረታቻ ሥርዓት የመቅረጽ ስራ ተሰርቶ የምስጋና ምስክር ወረቀትና ማበረታቻ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ የዐቃቤ ህግ የደረጃ እና እርከን መሰላል እና ጥቅማጥቅም መወሰኛ መመሪያ አዘጋጅተን ጸድቆ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ እንዲሁም የሰው ሀይልን አቅም በአጫጭር እና የረጅም

ጊዜ ስልጠና ፕሮግራሞች አቅም ከማሳደግ ጎን ለጎን የአመራሩንና የባለሙያውን አመለካከት ዕውቀት፣ ክህሎትና የስነ-ምግባር ጉድለቶች በመለየት በየደረጃው የሚገኙ 81 አመራሮች የማጥራትና 53 ባለሙዎች ላይ ደግሞ የዲሲፕሊን ጉዳዮችን በማጣራት እርምጃ የመውሰድ የማረምና የማስተካከል ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

ይሁን እንጂ ከላይ የተገለፁት አበረታች የለውጥ ስራዎች ቢኖሩም አሁንም ተጀምረው ያልተጠናቀቁ እና ተጠናቀው በተሟላ ሁኔታ ወደ ትግበራ ያልተሸጋገሩ አሰራሮች መኖራቸው፣ አንዳንድ የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አምዶች (የመሰረተ ማህበረሰብ ፍትህ አገልግሎት፣ የብዝሃ ህግ እና አማራጭ የፍትህ መስጫ ስርዓቶች) የተግባራት ግልፅነት ችግር መታየቱ፣ እንዲሁም በግጭት ውስጥ እንደቆየና አሁንም ከግጭት አዙሪት እንዳልወጣ ክልል በአመራሩ በባለሙያውና በህበረተሰቡ መሰራት ያለባቸው ስራዎች በመለየት የአሰራር ስዓቶችን ማጠናቀቅና ወደ ትግበራ ማሸጋገር ይገባል፡፡

## 2. የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን ተግባራዊ ማድረግ በተመለከተ

የሽግግር ፍትህ ሥርዓትን መተግበር ለሰብዓዊ መብቶች መከበር እና ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ በሀገሪቱ በተከሰቱ አለመግባባቶች እና ግጭቶች ምክንያት አለመረጋጋት፣ መጠነ-ሰፊ እና ተከታታይ መፈናቀል እና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ሲፈፀሙ ይስተዋላሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በሀገር ደረጃ ተቀርፆ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ የፖሊሲው ስልቶች የሆኑትን የወንጀል ፍትሕን ማስፈን፣ እውነትን መፈለግ እና ይፋ ማውጣት፣ የእርቅ ተግባራት፣ ማካካሻ እና ተቋማዊ ማሻሻያዎችን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ በክልሉ ለመተግበር የቢሮው ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ አኳያ ስለ ሽግግር ፍትህ አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ተግባሩ በዚህ ዓመትም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

## 3. አስተዳደራዊ ፍትህን በተመለከተ

አስተዳደራዊ ፍትህ የማህበራዊ ፍትህ የማእዘን ድንጋይ ነው፡፡ አስተዳደራዊ ፍትህ ምናልባትም ከወንጀል እና ከፍትሐብሔር ክርክሮች በላይ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን የእለት ተእለት ኑሮ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድር የፍትህ ዘርፍ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ዜጎች የመንግስት አሰራር በግልጽ የሚከታተሉበት እና ጥቅማቸውን በሚጎዱ የመንግስት ውሳኔዎች በቀጥታ ተሳታፊ የሚሆኑበት እንዲሁም በህግ ጥበቃ የተደረጉላቸው መብቶቻቸው ላይ ጥሰት የሚፈጽሙ የመንግስት አካላትን እና ውሳኔዎቻቸውን ተቃውመው በፍርድ ሂደት

መፍትሄ የሚያገኙበትን የህግ ስርአት መፍጠር ነው፡፡ በዚህም መሰረት የአስተዳደር ሥነ-ስርዓት ህግ እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን በህጉ ላይ የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎች መስራት፣ በአስተዳደር ተቋማት የሚወጡ መመሪያዎችን መርምሮ የመመዝገብ፣ ዌብሳይት ላይ የመጫንና ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ተደራሽ ማድረግ፣ ተግባራዊነታቸውን የመከታተል ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ቢሮው በቀጣይም ተግባሩን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

## 4. ከተቋማዊ የመፈጸም አቅም አንጻር፤

የፍትህ ቢሮን የመፈጸም አቅም ከማሻሻል እና ከማሳደግ አንጻር ተቋማዊ አደረጃጀትን በየደረጃው በሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች ቢሮው በቢሮ ኃላፊ ዘርፍ፣ በጠቅላይ ዓቃቢ ሕግ ዘርፍ እና በሕግና ፍትሕ ዘርፍ የተደራጀ ሲሆን በ5 ቋሚ ምድብ ማስ/ ጽ/ቤቶች፣ በ14 ፍትህ መምሪያዎች፣ በ164 የወረዳ ፍትህ ጽ/ቤቶች እና በ38 ንዑስ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤቶች ተደራጅቷል፡፡ በእነዚህ ተቋማትም 1,831 ዐቃብያነ-ህግና ተሿሚዎች እንዲሁም 1,731 የአስተዳደር ሰራተኞች በጠቅላላው 3,562 የሰው ሀይል በመያዝ ስራው እተከናወነ ይገኛል፡፡

ከአቅም ግንባታ ስራ ጋር ተያይዞም በበጀት ዓመቱ ለ1,201 ዐቃብያነ-ህግና አስተዳደር ሰራተኞች ክፍተትን የለየ የተለያዩ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም ከመንግስት ከሚመደበዉ በጀት ሌላ ከአገር ዉስጥና ከዉጭ አገር ድጋፍ ብር 20.1 ሚሊየን ብር ለማሰባሰብና ስራ ላይ ለማዋል ተችሏል፡፡

ይሁን እንጅ በተቋሙ መዋቅራዊ የአደረጃጀት ክፍተቶች መኖር እና እስከታች ባሉ መምሪያና ጽ/ቤቶች ከስራው ፍሰት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሰው ኃይል እና ተቋማዊ የተደራሽነት ችግር ለመፍታት የተጀመረውን ተቋማዊ የአደረጃጀትና የአሰራር ማንዋል በማጠናቀቅ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

የፍትህ ዘርፍ ተቋማት አደረጃጀትን ማስተካከልና ዘርፉን ሳቢና ታማኝነት የተቸረዉ ማድረግን በተመለከተም የክልሉ ፍትህ ቢሮን ህንጻ ሙሉ በሙሉ የማደስ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸውን የዞንና ወረዳ ተቋማት መልሶ ለማቋቋም ከክልሉ መንግስት የቢሮ ጥገና በጀት ተመድቦ  አንድ ዞን ፍትህ መምሪያና 14 ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤቶች ጥገና በማድረግ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ በአብዛኞቹ ዞኖች የተሻለ የሕንፃ መሰረተ-ልማት የተገነባላቸውና በአዲስ በመገንባት ያሉ መሆኑ፣ በወረዳ ደረጃም አንዳንድ ወረዳዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ቢሮዎች  በመገንባት ወደ ስራ መግባታቸው ጅምሩ ጥሩ ቢሆንም ከቢሮ እስከ ወረዳ ድረስ ያሉ ሁሉም ተቋሞቻችን የቢሮ እና ሌሎች የግብአት ችግሮች በተፈለገው ደረጃ አልተፈታም፡፡  ከዚህም ባሻገር የበጀት እና የግብዓት ችግር አሁንም ትልቅ ማነቆ ሆኖ መቀጠሉ ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ እንዳይፈፅም አድርጎታል፡፡

### 5. ተቋማዊና ሙያዊ ነፃነት እና ገለልተኝነትን ከማረጋገጥ አኳያ፤

ዐቃብያነ ህግ ከማንኛውም አካል ጣልቃገብነትና ተጽዕኖ ነጻ ሆነው እንዲሁም ሙያዊ ገለልተኝነታቸውን ጠብቀው መስራት እንዳለባቸው በህግ ተደንግጓል፡፡ ይህን በተሟላ ሁኔታ እንዲከበር ለማድረግ በርካታ የህግ ማዕቀፎች፣ አሰራሮች እና አደረጃጀቶች መኖራቸው፣ መንግስትም ዐቃብያነ-ህግ ነጻና ገለልተኛ ሆነው እንዲሰሩ የሚያሳየው ጅምር እንቅስቃሴ በበጎ ጎኑ የሚወሰድ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ከዓቃቤ ህግ ተቋማዊ የተግባር እና ሙያዊ ነጻነት ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ችግሮች አሉ ለአብነትም፡- የሰው ሃብትና የበጀት አስተዳደር ነጻነት በተሟላ ሁኔታ አለመረጋገጥ፣ ገለልተኛ የሆነ የጠቅላይ ዓቃቤ ህግ አደረጃጀትን ማስቀጠል አለመቻሉ፣ የዓቃብያነ ህግ ሙያዊ ነጻነት ያለመከበር ችግር ያለ ሲሆን እነዚህን ችግሮች በመፍታት ከተቋሙ የሚጠበቀውን የላቀ ውጤት ማስመዝገብ ተገቢ ይሆናል፡፡

### 6. የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ቅልጥፍናን እና ጥራትን ከማረጋገጥ አኳያ፤

ቢሮው በአዋጅ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች አኳያ በወንጀል ፍትህ አስተተዳዳር፣ በፍትሐብሄር ፍትህ አስተዳደር የተከናወኑ ተግባራት አፈጻጸም እና የአገልግሎት አሰጣጥና ቅልጥፍናን በተመለከተ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

**የወንጀል ፍትህ አስተዳደር /ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ/ ዘርፍ፡-** ይህ ዘርፍ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች፣ የመደበኛ ወንጀል ጉዳዮች፣ የኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች እና የሐብት ማስመለስ ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን ዋና ስልጣን እና ተግባሩም ወንጀል ምርመራን መምራት፣ የክስ እና ክርክር አገልግሎት፣ በወንጀል የተገኘ ንብረት ማስመለስ እና በሂደቱ ጉዳዮች ፍርድ ቤት ከመድረሳቸው በፊት የማጥራት እና ውሳኔ መስጠትን የሚያጠቃልል ሲሆን ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን ወንጀል ጉዳዮችን ለይቶ መስራት፣ የመዛግብት ማጥራት ምጣኔ፣ በቀጥታ ክስ ተከራክሮ አጥፊዎችን የማስቀጣት ምጣኔ፣ የወንጀል ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ እና የይግባኝ እና ሰበር የማሸነፍ ምጣኔ የተሻለ አፈፃፀም አስመዝግቧል፡፡ በዚህ መሰረትም የመዝገብ ማጥራት ምጣኔን 98.71 በመቶና ተከራክሮ የማሸነፍ ምጣኔን 89.27 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በወንጀል የተገኘ ሀብትን በማስመለስ ረገድ ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት ለማስመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡

ይሕ ዘርፍ ካሉበት በርካታ ውስብስብ ችግሮች አንጻር የተመዘገበው ውጤት ሲታይ አፈጻጸሙ ጥሩ ደረጃ ላይ ቢሆንም ምርመራን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ከመምራት ጀምሮ የወንጀል እና ወንጀለኛ መረጃ አያያዝ፣ ከፖሊስ እና ፍርድ ቤት ጋር የመረጃ ልውውጥ እና ትስስር አለመፍጠር፣ የምርመራ ጥራት ችግርን አለመሻገር፣ የመዛግብት የመቋረጥ ምጣኔን ዝቅ

ያለማድረግ፣ የክስ እና የክርክር ጥራት ችግር በዘላቂነት አለመፍታት፣ የኤግዚቪት አያያዝ፣ አስተዳደርና አመላለስ ላይ የሚታየውን ችግር በዘለቄታ አለመፍታት፣ የገንዘብ ቅጣት በተገቢው ሁኔታ አለማስፈጸም፣ በወንጀል ምክንያት የተወሰደን ንብረት በተፈለገው ደረጃ አለማስመለስ እና በዘርፉ ላይ የሚታዩ የአደረጃጀት ችግሮችን አለማስተካከል ዋናዋና ችግሮች ስለሆኑ እነዚህን ችግሮች ሊፈታ የሚችል ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

**የሕግ እና ፍትሕ አግልግሎት ዘርፍ፡-** ይሕ ዘርፍ የፍትሐብሄር ፍትሕ አስተዳደር አገልግሎት፣ የሰነዶች፣ ጠበቆች እና ሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶች ምዝገባ፣ ማረጋገጥ እና ክትትል አገልግሎት፣ የሕግ ማርቀቅ፣ ምክርና ማጠቃለል አገልግሎት እና የሰብአዊ መብት ክትትል አገልግሎት የሚያጠቃልል ሲሆን ቢሮው የክልሉ መንግስት ዋና የሕግ እና ፍትሕ አማካሪ በመሆን ከሚወጡ ሕጎች ፍትሐዊነት ጀምሮ እስከ አፈጻጸም ድረስ የክልሉን መንግስት እና ሕዝብ ጥቅም እና መብት መከበሩን በማረጋገጥ ተግባራትን በመፈፀም ላይ ይገኛል፡፡ በፍትሕብሄር ፍትሕ አስተዳደር ጉዳዮች የመዛግብት የማጥራት ምጣኔ፣ በቀጥታ ክስ ተከራክሮ የመርታት ምጣኔ፣ ውል ምርመራ፣ የህግ ምክር እና የውል ሰነድ ዝግጅት፣ በድርድር መዛግብትን የመቋጨት ምጣኔ አፈጻጸም የተሻለ አፈፃፀም የተመዘገበበት ነው፡፡

በዚህ መሰረትም የመዝገብ ማጥራት ምጣኔን 98.9 በመቶ፤ የማሸነፍ ምጣኔን 90.0 በመቶና ፍርድ የማስፈጸም ምጣኔ 97.98 በመቶ ደርሷል፡፡ በአፈፃፀም ገቢ መሆን የሚገባውን ገንዘብ አሟጦ ገቢ ያለማድረግ ክፍተት፣ ነጻ-የህግ አገልግሎትን በስፋት ከመስጠት አኳያ ክፍተቶች ያሉ በመሆኑ በቀጣይ ይህንን አፈጻጸም ሊያሳድግ የሚችል ስራ መስራት ይጠይቃል፡፡

**የሕግ ማርቀቅ፣ ምክርና ማጠቃለል ስራዎችን በተመለከተ፡-** የክልሉን አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ችግሮች በጥናት በመለየት የማሻሻል ስራ ከመሰራቱ በተጨማሪ በተሻሻለው አዋጅ መሰረት ለተቋቋሙ ተቋማት ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ ደንብ የማዘጋጀትና የማስጸደቅ፣ ሌሎች የተቋማት አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው የተላኩ ሲሆን የሚዘጋጁ ሕጎችን ጥራት ለማስበቅ የሕግ አወጣጥ ማንዋል ተዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት በበጀት አመቱ አጠቃላይ 96 ህጎች ተዘጋጅተዋል፡፡ በተጨማሪም 135 መመሪያዎችን ሕጋዊነት በመመርመር የመመዝብ እና ዌብሳይት ላይ የመጫን ስራ መሰራቱ እና በክልሉ የወጡና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ ህግጋትን የማጠቃለል ስራ መሰራቱ እንዲሁም ለቀረቡ የክልሉ ተቋማት የሕግ ምክር መሰጠቱ በጥንካሬ የሚታይ ሲሆኑ በተወሰኑ ሕግጋት ላይ የጥራት ችግሮች የሚታዩ መሆኑ፣ አልፎ አልፎም ቢሆን በተሰጡ የሕግ ምክሮች

ላይ የትንታኔ ጥልቀት ውስንነት ያለባቸው በመሆኑ እነዚህን ችግሮች በቀጣይ ማሻሻል ይጠይቃል፡፡

**የሰነዶች፣ ጠበቆች እና ሲቭል ማሕበረሰብ ድርጅቶችን በተመለከተ** የሰነዶች አገልግሎትን ለማዘመን የሰነዶች ምዝገባ በሀገር አቀፍ ደረጃ የለማውን Daris ሶፍትዌር ጥቅም ላይ ማዋል መጀመሩ፣ በክልል ደረጃ ተግባራዊ እየተደረገ በሚገኘው የአንድ ማዕከል የመሶብ አገልግሎት የሰነዶች አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉ፣ በጀት ዓመቱ ለ266,855 ልዩ ልዩ ሰነዶች ምዝገባ በማድረግ የቀረበውን 100% አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡

በተሻሻለው የጠበቆች አዋጅ መሰረት የጠበቆች ማህበር በአዲስ መደራጀቱ እና ለጠበቆች የሙያ ስልጠና መሰጠቱ፣ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች የመመዝገብ፣ የመከታተል ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል የታየበት መሆኑ እና የጋራ ምክር ቤት መቋቋሙ አገልግሎቱን በተደራጀ መንገድ ለመምራትና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ምቹ ሁኔታ የተፈጠረ ቢሆንም የሰነዶች ምዝገባን በሚፈለገው ልክ በቴክኖሎጂ በመደገፍ እና አገልግሎቱን ተደራሽ በማድረግ እንዲሁም ጠበቆች በፍትህ ስርአቱ ውስጥ አዎንታዊ ሚና እንዲኖራቸው በማድረግ እና በአግባቡ የማስተዳደር ውስንነት የሚታይበት መሆኑ፣ የሲቭል ማሕበረሰብ ድርጅቶችን መረጃ አደራጅቶ የመያዝ ክፍተት ያለ በመሆኑ በቀጣይ የአገልግሎት ጥራት እና ቅልጥፍናን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

**ሰብዓዊ መብትን በማስከበር ረገድ**:- ሰብአዊ መብትን ከማሳወቅ፣ ከማክበር እና ከማስከበር አኳያ በማረሚያ ቤት እና በፖሊስ ጣቢያ የሚገኙ  በጥበቃ ስር ያሉ  ታራሚዎች ወቅቱን ጠብቆ ጉብኝት የማድረግ፣ ከፖሊስ እና ማረሚያ ቤት ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት የሚደርሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና ጥቆማዎችን የማጣራት እና የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ጥረት የተደረገ ቢሆንም በክልሉ በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ምክንያት በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት በተሟላ ሁኔታ ከማስከበር አኳያ ክፍተት ስለሚታይ የተፈጠረውን ክልላዊ የጸጥታ ችግር በአፋጣኝ በመፍታት በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥስት መከላከልና በፖሊስ እና ማረሚያ ቤቶችን በመጎብኘትና ከህግ ውጪ የታሰሩ ዜጎች ላይ አፋጣኝ ምርመራ በማድረግ መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በሰዎች የመነገድና ሰዎችን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ከመከላከል አኳያ የፍልሰት አስተዳደርና አሰራር ሥርዓት መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ መፅደቁ እና አደረጃጀቶችን የማጠናከር ስራ የተሰራ ቢሆንም ለፍልሰት ተጎጂዎች በተቀናጀ ሁኔታ

ምላሽ በመስጠት በኩል ክፍተት ያለ በመሆኑ በቀጣይ አደረጃጀቱን ወደታች በማውረድ ለፍልሰት ለተጎጂዎች በተቀናጀ ሁኔታ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚደርሱ የኃይል ጥቃቶች ለመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት፣ ተግባራትን የመገምገም፣ ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶችና ህፃናት በአንድ ማዕከል አገልገሎት ምላሽ የመስጠት ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም በአንድ ማዕከል የሚሰጡ አገልግሎቶች ተደራሽ አለመሆንና ያሉትም ቢሆን የተሟላ አገልግሎት ያለመስጠት የአሰራር ክፍተቶች የሚታዩ ስለሆነ  በቀጣይ ይህንን ችግር ሊፈታ የሚችል ስራ መስራት ይጠበቃል፡፡

**በወንጀል እና በፍትሐብሄር ፍትህ አስተዳደር ዘርፍ  የአቤቱታ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ** በተለያዩ ጊዜያት ከመንግሥታዊ የአስተዳደር ተቋማት ከሚደርስ አስተዳደራዊ በደል የመነጨ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በሰፊው የሚነሱበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ስለሆነም ለቢሮው የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ለመፍታት በተደረገ ጥረት በወንጀል እና ፍትሐብሔር ጉዳዮች የቀረቡ አቤቱታዎችን በተገቢው መንገድ ምላሽ መስጠት የተቻለ ቢሆንም ተፈፃሚነቱን በማረጋገጥ ረገድ ውስንኖች ይስተዋላል፡፡ ስለሆነም በፍትህ አስተዳደር ዘርፉ የሚቀርቡ አቤቱታዎች በወቅቱና አፋጣኝ መፍትሄ የመስጠት እና ተፈፃሚነታቸውን የማረጋገጥ ስራ ተጠናክሮ መስራት ይገባል፡፡

**ይቅርታ አሰጣጥን በተመለከተ፡-** የይቅርታ አዋጁን መሰረት በማድረግ 1,224 ለሚደርሱ ታራሚዎች ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ተችሏል፡፡ የይቅርታ አሰጣጥ ማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለውሳኔ ቀርቧል፡፡ ይሁን እንጂ የይቅርታ ተጠቃሚ ታራሚዎች ጉዳይ በአግባቡ የማይጣራ መሆኑ፣ በይቅርታ ቦርድ በኩል የቀረቡ የይቅርታ ውሳኔ ሀሳቦች በሚመለከተው አካል በወቅቱ ውሳኔ የማይሰጥባቸው መሆኑ፣ መስፈርት ሳያሟሉ እና በሀሰተኛ ማስረጃ የይቅርታ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ሊታረም የሚገባው ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የህግ ታራሚዎች በእርምት ወቅት የስነ-ምግባርቸውን ሁኔታ እና የይቅርታ መስፈርቱን ስለማሟላታቸው በአግባቡ በማጣራት ወቅቱን የጠበቀ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**7. የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ ፤**

በፍትህ ተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎችን ከማዘመንና ቴክኖሎጂን ከመጠቀም አኳያ ከክልሉ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ ጋር በመተባበር የፍትህ ተቋማት የተቀናጀ የፍትህ ስርዓት፣ የመረጃ ዳታ ቤዝ፣ ዌብሳይት፣ DARIS የማልማትና ወደ ትግበራ የማሸጋገር ስራ መሰራቱ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ኮሙኑኬሽን ቴክኖሎጂ አደረጃጀት እስከ ዞን እና ከተማ አስተዳደሮች

ድረስ መፈቀዱና ፈጣንና ዉጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ጅምር ስራ ተሰርቷል፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ስራ የተሰራ ቢሆንም አሁንም የፍትህ ተቋማቱ በቴክኖሎጂ አቅርቦትም ሆነ አጠቃቀም ረገድ ውስንነት ያላባቸው በመሆኑ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠይቃል፡፡

**8. የህብረተሰብ ግንዛቤና ተሳትፎን በተመለከተ፡-**

የማህበረሰብ የህግ ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች 1,854,508 ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ንቃተ ህግ የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ለመስጠት ጥረት መደረጉ፣ ለ59 የወንጀል ጠቋሚዎች እና ምስክሮች ጥበቃ/ከላላ የመስጠት ስራ መሰራቱ፣ ማህበረሰቡ በፍትህ ተቋማቱ ላይ ያለውን ቅሬታና ጥቆማ የሚሰጥበት ግልጽ ስርዓት መፈጠሩ፣ በጥንካሬ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የህዝብ ቅሬታዎችን ለመለየት የሚያስችሉ የምክክር እና የውይይት መድረኮችን በየደረጃው አለመከናወኑ፣ ለወንጀል ተጎጂዎች፣ ለጠቋሚዎች እና ምስክሮች ወጥ የሆነ የጥበቃ ስርዓት መዘርጋት አለመቻሉ፣ የማረም እና የማነጽ ተግባር ማህበረሰብ ተኮር አማራጮችን ያላካተተ እና ማህበረሰብን ያላሳተፈ መሆኑ በውስንነት የተስተዋሉ ናቸው፡፡

**9. ተደራሽነትን ከማሳደግ አኳያ፤**

የተቋማቱን አካላዊ ተደራሽነት ለማስፋት በተያዘው ዕቅድ መሰረት 5 ቋሚ ምድብ ማስ/ጽ/ቤቶች፤ በወረዳ እና እንደአስፈላጊነቱ እስከ ንዑስ ወረዳ ድረስ ስራዎች ተደራሽ ሆነዋል፣ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ስልጠና መስጠትና የማጠናከር ስራ ጅምር እንቅስቃሴ መኖሩ፣ ከአገልግሎት ተደራሽነት አንጻርም ወደ ማህበረሰቡ በመውረድ መስራት፤ የመክፈል አቅም ለሌላቸው ለሴቶች፣ ለህጻናት እና አቅመ ደካማ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ነጻ የህግ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት መቻሉ በጥንካሬ የታዩ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ ሴቶች፣ ህጻናት፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች የወንጀል ሰለባ ሲሆኑ እና ለመብት ጥሰት ሲጋለጡ አገልግሎቱን በሚፈለገው ደረጃ በመስጠት በኩል ውስንነት የሚታይበት መሆኑ እና የህጻናት ጊዜያዊ ማቆያ ተቋም በበቂ ሁኔታ አለመኖር ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

**10.ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ**

የፍትሕ አገልግሎት በአንዱ ተቋም ተጀምሮ እዚያው የሚያልቅ አይደለም፡፡ ስለሆነም የዘርፉን ተቋማት ቅንጅትና የእርስ በእስርስ ትብብር ይጠይቃል፡፡ የዘርፉ ተቋማት በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሄር ዘርፉ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት ጥረት መደረጉ፣

ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ስራዎችን በጋራ የመገምገምና የድጋፍ ስራዎች መስራት መቻሉ ማለትም ከምርመራ እስከ ፍርድ አሰጣጥ ያለዉን የወንጀል ጉዳዮች ችግር ለመፍታት የሚያስችል መግባቢያ ሰነድ የአብክመ ፍትህ ቢሮ እና ፖሊስ ዋና ጠቅላይ መምሪያ መካከል የተደረገ ስምምነት፤ የሙስና ወንጀሎችን በጋራ ለመከላከል የሚያስችል የአብክመ ፍትህ ቢሮና የስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን መካከል የተደረገ ስምምነት፤ ሃብት የማስመለስ ስራን ዉጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ከ18 የክልልና የፌደራል ተቋማት ጋር የተደረገ ስምምነት፤ ህግ ወጥ ንግድና ኮንትሮባንንድን ለመከላከል ከ13 የፌደራልና የክልል ተቋማት ጋር የተደረገ ስምምነት መደረጉ፣ ልዩ ትኩረት በሚያስፈልጋቸው የወንጀል ጉዳዮችን በቡድን የማጣራት ስራ መሰራቱ፣ የነፃ ህግ ድጋፍ ፎረም መመስረቱ፣ የዳኝነት እና የፍትሕ አካላት የትብብር መድረክ የተጀመሩ ስራዎች አበረታች ናቸው፡፡

ሆኖም ግን በዘርፉ ተቋማት መካከል የትብብር መድረኮችን ቀጣይነት ባለው መልኩ ተግባራዊ ማድረግ ባለመቻሉ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም የባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ ስራዎች አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል፡፡

## 3. ርዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች

- **ርዕይ**

በ2022 የሕዝብ አመኔታ ያለው እና በሀገር ደረጃ ተምሳሌት የሆነ የፍትሕ ተቋም ሆኖ ማየት

- **ተልዕኮ**

የህግ የበላይነትንና ሰብዓዊ መብትን በማክበርና በማስከበር፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥና የመንግስትንና የህዝብን ጥቅም በማስጠበቅ፤ የሕዝብ ዓመኔታ ያተረፈ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ የፍትህ አገልግሎት መስጠት፡፡

- **ተቋማዊ እሴቶች**

1. ያለ ክንፍ መብረር ያለ ሙያ መክበር አይቻልምና **በሙያ ብቃት** እንክበር፤
2. መታዘዝ ከመስዋዕትነት ይበልጣልና ምርጫችን **አገልጋይነት** ነው፤
3. የሰው ወርቅ አያደምቅምና **በራሳችን ባህል** እንደምቃለን፤ እንጠበቃለን፤
4. አበው በህግ አምላክ ብለው እንደተገዙለት እኛም **ለህግ እንገዛለን**፤
5. ከባህር የወጣ ዓሳ ላለመሆን **ሕዝባዊ ወገንተኝነትን** አጥብቀናል፤
6. ከመቃብር በላይ ስም ይቆማልና **አርበኝነት** መለያችን ነው፤
7. ብልህ የዓመቱን፣ ሞኝ የእለቱን ነውና እንደ ብልሆች **ሀብትን በአግባቡ ቆጥበን እንጠቀማለን**፤

8. መልካም ሃሳብ ወንዝ ያሻግራልና **ልዕለ ሐሳብ ይገዛናል፤**
9. መድረሻውን ያላወቀ የትም ይገኛልና **ትኩረታችን ለግቦቻችን** ይሁን ብለናል፤
10. ልዩነታችን ውበት ነውና **ብዝሐነት ተቀብለናል፤**
11. ቋጠሮ መፍታት ከውሉ እንዲሉ **ምርምርና ፈጠራን** ለችግራችን መፍቻ አድርገናል፤
12. ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር ነውና **ቅንጅታዊ አሠራር** እሴታችን ነው፤
13. አለባበሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ በመሆኑ **ግልፅነትና ተጠያቂነት** እሴታችን ነው።

# 4. ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች፣ የትኩረት መስኮች፣ የትኩረት አቅጣጫዎች፣

## 4.1. ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች

1. የህግ የበላይነት አለመረጋገጥ
2. የሙያዊ ብቃት ችግር
3. የስነ-ምግባር እና ተጠያቂነት ችግር
4. የሰብአዊ መብቶች በሚጠበቀው ደረጃ አለመከበር
5. የአገልገሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናና ጥራት ችግር

## 4.2. የትኩረት መስክ

በቢሮዉ የሚሳኩ ግቦችና የሚከናወኑ ተግባራት በተቋሙ የተለዩ አራት ተቋማዊ ስትራቴጂካዊ መስኮች እና ውጤቶች መሰረት ሲሆን እነዚህም፡-

1. የሕግ የበላይነት ማረጋገጥ
2. የላቀ ፍትሕ አገልግሎት
3. ሰብአዊ መብት ማክበርና መስከበር
4. ሙያዊ ብቃትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ

| ተ.ቁ. | ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ /Strategic Themes/ | ስትራቴጂያዊ ውጤት /Strategic Result/ |
|---|---|---|
| 1 | የህግ በላይነትን ማረጋገጥ | የተረጋገጠ የህግ የበላይነት |
| 2 | የላቀ የፍትህ አገልግሎት | በአገልግሎቱ የተገልጋይ እርካታ |
| 3 | የሰብዓዊ መብትን ማክበርና ማስከበር | የሰብአዊ መብት አያያዝ እና ጥበቃ |
| 4 | ሙያዊ ብቃትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ | ያደገ ሙያዊ ስነምግባር |

### የትኩረት መስኮች መግለጫ

**የህግ በላይነትን ማረጋገጥ፡–** ቢሮዉ ከተቋቋመበት አላማዎች መካከል የህግጋትን ተፈጻሚነት በማረጋገጥ የህግ የበላይነትን ማስፈን አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ የሕግ የበላይነት ማለት ማናቸውም የመንግሥት አካል፣ ባለሥልጣን፣ የግልም ሆነ የመንግሥት ድርጅት እንዲሁም ማናቸውም ግለሰብ የአገሪቱን ሕግ ማክበር እንዳለበትና የትኛውም ወገን ከሕግ በታች እንጅ በላይ እንዳልሆነ የሚያመለክት ሲሆን ከዚህም በመነሳት የላቀ የህጎች ተፈፃሚነት የተቋሙ የትኩረት መስክ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

**የላቀ የፍትህ አገልግሎት፡-** የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ በሕግ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች አንጻር በርካታ አገልግሎት የሚሰጣቸው ተገልጋዮች አሉ፡፡ እነዚህ ተገልጋዮች እንደየአገልግሎቱ ዓይነት እና ባህሪ የተለያዩ ፍላጎቶች ያሏቸው ቢሆንም በጥቅል ሲታይ ግን ተቋሙ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ፍትሐዊና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ፣ ጥራት ባለው፣ ምልልስና ኣላስፈላጊ ዉጣ ዉረድን በመቀነስ እንዲሁም በቅርበት እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ፡፡ በመሆኑም በአጠቃላይ ተገልጋዮችከተቋሙ ተግባርና ኃላፊነት ጋር በተገናኘ አገልግሎት በሚጠይቁበት ወቅት አላስፈላጊ የሆኑ የቅብብሎሽና የምልልስ አሠራሮችን በመቀነስ፣ ለተገልጋዮች እሴት የማይጨምሩ ሥራዎችን በማስወገድ፣ ሥራዎቹ እሴት የሚጨምሩ ቢሆን እንኳን በተፋጠነ እና በጥራት እዲሠሩ በማድረግ፣ ለፈጻሚዎች ተጨማሪ ኃላፊነቶችን ተጠያቂነት ጋር በመስጠት፣ በአነስተኛ ወጪና በተፋጠነ መልኩ ያለ እንግልት ተገልጋዮች ተደራሽ የሆነ የፍትሕ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ የላቀ የፍትህ አገልግሎት መስጠት እና ተደራሽነት የተቋሙ የትኩረት መስከ ይሆናል፡፡ በዚህ መስክ ላይ አተኩሮ መሥራቱ ተቋሙ የሚሰጣቸው የፍትህ አገልግሎቶች ጥራት ያላቸው፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ በማድረግ ተቋሙ ራዕዩንና ተልዕኮውን እንዲወጣ ከማስቻሉም በላይ የተገልጋዩን እርካታ ያረጋግጣል፡፡

**ሰብዓዊ መብትን ማክበርና ማስከበር፤-** ሰብዓዊ መብት ሰዎች ሰው በመሆናቸው ሊያገኙት የሚገባ የማይጣስ እና የማይገሰሱ መብቶች ሲሆኑ የዜጎችን መብት የማስከበር ስርዓት ሊረጋገጥ የሚችለው ተቋማት በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት ሰዎች በህግ በተረጋገጠ አግባብ መብቶቻቸው ተጠብቀው ሲገኙ ነው፡፡ በመሆኑም የሰብዓዊ መብት መከበር ለአንድ ተቋም ብቻ ሚሰጥ ሳይሆን ሁሉም አካላት የበኩሉን ድርሻ መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም የሰብዓዊ መብት አያያዝን በማጠናከር ዜጎች ለህገራዊ ልማት ሊኖራቸው ሚችለውን አስተዋፅኦ ለማጎልበት እና መብቶቻቸው ተጥሰው ሲገኙ ተገቢውን የማጣራት ስራ በመስራት ሰብዓዊ ክብርን ማስጠበቅ በትኩረት የሚሰራበት ይሆናል፡፡

**ሙያዊ ብቃትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፡-** የፍትህ ስርዓቱ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣

ፍትሃዊ እንዲሆን ለማድረግ የፈፃሚው ሙያዊ ብቃት ማሳደግ፣ ግልጸኝነት የሰፈነበት፣ ስነምግባር የተላበሰ አገልግሎት መስጠት የሚያስፈልግ ሲሆን የተቋሙን ውጤታማነት ለማሳደግ እንዲቻል የተጠያቂነት አሰራርን ማረጋገጥ በተግባር የሚሰራበት ይሆናል፡፡

### 4.3. የትኩረት አቅጣጫዎች

የህግ የበላይነትን በማስከበር የክልሉን ሠላምና የህዝቡን ደህንነት ማረጋገጥ አንዱ ወሳኝ የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን ተቋማዊ አቅምን መገንባት፣ የህብረተሰቡን የንቃተ ህግ ግንዛቤን ማሳደግ እንዲሁም የፍትህ ተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራር ማሳደግ የሚሉትም ተለይተዋል፡፡ በተመሳሳይ የፍትህ ተቋማትን ነጻነትና የሙያ አገልግሎት የተሟላ ማድረግ፣ ማህበራዊ ሀብቶችን፣ እሴቶችንና አካባቢያዊ ዕውቀቶችን ማሳደግ፣ ህግ የማስከበርና የሰብዓዊ ደህንነት አቅምንና ተዓማኒነትን ማሳደግ፣ በክልሉ የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ የሰብዓዊ መብት ማክበር እና ማስከበርን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ የፍትህ ስርዓቱ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ፍትሃዊና ግልጸኝነት የሰፈነበት እንዲሆን ማስቻል እንዲሁም የሙያ ብቃትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ የሚሉት የዘርፉ የበጀት ዓመቱ ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫዎች ሆነው ተቀምጠዋል፡፡

## 5. ዓላማ፣ ስትራቴጂክ ግቦች እና ተግባራት

### 5.1. ዓላማ

☞ ሕገ መንግስቱንና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በማክበርና በማስከበር የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ እና የመንግስትና የህዝብ መብትና ጥቅሞችን ማስጠበቅ፡፡

### 5.2. ዋና ዋና ግቦች /strategic Objectives/

☞ ሁሉንም የዘርፉን የትኩረት መስኮችን ታሳቢ ያደረጉት 14 የተጠቃለሉ ዋና ዋና ግቦች፡-

| ተ.ቁ. | ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ | ስትራቴጂያዊ ውጤት /Strategic Result/ | ዋና ዋና ግቦች/strategic Objectives |
|---|---|---|---|
| 1 | የህግ በላይነትን ማረጋገጥ | በተረጋገጠ የሕግ የበላይነት | 1. የሰው ሀብት ልማት እና ተቋማዊ አቅም ግንባታ፤<br>2. ውጤታማ የቴክኖሎጂ አቅርቦት እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣<br>3. የአገልግሎት ቅልጥፍና፣ ጥራት እና ውጤታማነትን በማሳደግ የተገልጋይ እርካታን መጨመር፤<br>4. ተቋማት ሙያዊ ነፃነት፣ ገለልተኝነት እና ተጠያቂነትን |
| 2 | የላቀ የፍትህ አገልግሎት | በአገልግሎቱ የተገልጋይ እርካታ | |
| 3 | የሰብኣዊ መብትን ማክበበርና ማስከበር | የሰብኣዊ መብት አያያዝ እና ጥበቃ | |

| ተ.ቁ. | ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ | ስትራቴጂያዊ ውጤት /Strategic Result/ | ዋና ዋና ግቦች/strategic Objectives |
|---|---|---|---|
| 4 | ሙያዊ ብቃትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ | ያደገ ሙያዊ ስነምግባር | ማረጋገጥ፤<br>5. ቅንጅታዊ አሰራር ማሳደግ፤<br>6. የህብረተሰቡን ግንዛቤና ተሳትፎ በማሳደግ ብዝሃ-ሕግ እና አማራጭ ፍትሕ መስጫ ስርዓቶችን ማጠናከር፤<br>7. በፍትሐብሄር የፍትህ አስተዳደር የመንግስትና የህዝብ ጥቅሞችን ማስጠበቅ ዉጤታማነት ማሳደግ፤<br>8. የህግ አገልግሎት አሰጣጥ ዉጤታማነትን ማሳደግ፤<br>9. ተገማችና ፍትሃዊ የህግ አወጣጥ እና አፈጻጸም ዉጤታማነትን ማሳደግ፤<br>10. የአስተዳደር ፍትህን ዉጤታማነት ማሳደግ፤<br>11. የሰብአዊ መብትን ማሳዎቅ፣ ማክበር፣ማስከበር እና ማሟላት አፈፃፀምን ማሻሻል፤<br>12. የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውጤታማነትን ማሳደግ፤<br>13. የሴቶች፣ሕፃናት፣ ወጣቶች፤ አረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች እንዲሁም ለአደጋ ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ |

### 5.3. የ2019 በጀት ዓመት ግቦች

ከላይ የቀረቡ የትኩረት መስኮችን መሰረት አድርጎ የተቋሙን ዓላማ የሚያሳኩ ዋና ዋና ግቦች፣ ንዑስ ግቦች እና የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

**ግብ 1፡- የሰው ሀብት ልማት እና ተቋማዊ አቅም ግንባታ፤**

**የሚከናወኑ ተግባራት፤**

- ☞ ጥራት ያለው 1 ዓመታዊ እቅድ ማዘጋጀት፤
- ☞ ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ 5 የሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት፤
- ☞ ጥራት ያላቸው 4 የድጋፍና ክትትልና ግብረመልስ ተግባራዊ ማድረግ፤
- ☞ ወደ አመራር የመጡ ሴት ሰራተኞች ብዛት 11 በመቶ ማድረስ፤
- ☞ ግልፅነት የሰፈነበት የሰው ሀይል ስምሪትን 100% ጥራት እንዲኖረዉ ማድረግ፤
- ☞ የዐቃብያነ ህግ የመዝገብ ዉሳኔን ጥራት እና የክርክር ብቃት ለማሳደግ የሚያስችል 60 የህግ ኦዲት ስራ መስራት፤
- ☞ የአመራሮችን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ለማሳደግ የሚያስችል ስራን በትኩረት በመያዝ ለ230 አመራሮች የአጫጭር ጊዜ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣

- የፈጻሚዉን የመፈጸም አቅም ለማሳደግ የሚያስችል ስራን በጥብቅ በመያዝ ለ500 ዐቃብያነ ህግ እና የአስተዳደር ሰራተኞች የአጫጭር ጊዜ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
- የሴት ሰራተኞችን አቅም ለማሳደግ እንዲቻል ለ250 ሴት ሰራተኞች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
- አቅም ለመገንባት የረጅም ጊዜ ትምህርትና ስልጠና ለ20 ዐቃብያነ-ህግ እና አስ/ሰራተኞች መስጠት፣
- በውጤት የተመዘነ አመራር፣ ባለሙያ እና ሰራተኛ ለማፍራት ሁሉንም ሰራተኛ 100% በውጤት የመለካትን ተግባር መፈጸም፤
- የዘርፉን ሳቢነትና ማራኪነት ለመጨመር የሰራተኛ ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋትና መተግበር 1 ጊዜ፤
- የሰራተኛዉን ፍልሰት ለመቀነስ የሚያስችል ስራ በመስራት ፍልሰትን ከ1.82% ወደ 2.5% በመቀነስ የተቋማችንን የመፈጸም አቅም ማሳደግ
- ለቢሮ አገልግሎት የሚውል መስፈርትን ያሟላ ህንጻ 10% መገንባት፤
- ለተቋም አቅም ግንባታ በመንግስት የሚበጀተዉ በጀት በቂ ስለማይሆን በሀገር ውስጥ አጋርነት የሚገኝ ድጋፍን በማጠናከር ድርሻዉን 3 ሚሊየን ብር ማድረስ፤
- በውጭ ሀገር አጋርነት የተገኘ ድጋፍን ደግሞ 16 ሚሊየን ማድረስ፤
- የተመደበዉን መደበኛ በጀት 100% በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል፤
- የተመደበዉን ካፒታል በጀት 100% በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል፤
- የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን ወደ 0.3% መቀነስ፤
- ተከታታይ የኦዲት ስራ በመስራት ነቀፌታ ያለበትን የኦዲት ግኝት 100% መቀነስ፤

**ግብ 2፡-ውጤታማ የቴክኖሎጂ አቅርቦት እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የቴክኖሎጅ መሰረተ-ልማት ዝርጋታ በ10 በመቶ ማሟላት፣
- ኤሌክትሮኒክ ሕግ እና ፍትህ (e-Legislation and e-Justice) በ5 ፐርሰንት ተግባራዊ ማድረግ፣
- አንድ /1/ በቴክኖሎጂ የተደረገፈ የአፈፃፀም ምዘና ስርዓት መዘርጋት፤
- የተዘጋጀውን ኢንድ /1/ የተቋሙን የመረጃ ቋት ስራ ላይ ማዋል፤
- የተዘጋጀውን አንድ /1/ የተቋሙን ዌብሳይት በተገቢዉ ሁኔታ ስራ ላይ ማዋል፤
- ወረቀት አልባ አሰራርን 40% መተግበር ፣
- የሪፖርት እና መረጃ አያያዝን ድጅታላይዝድን 50% ማድረስ፤

**ግብ 3፡- የአገልግሎት ቅልጥፍና፣ ጥራት፣ ተደራሽነት እና ውጤታማነትን በማሳደግ የተገልጋይ እርካታን መጨመር፤**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ☞ የዓቃቤ ህግ አካላዊ ተደራሽነት ከስራው መጠንና ስፋት ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በበጀት አመታቱ 130 ተጨማሪ ዐቃብያሀ ህግ ማሰልጠንና ወደ ስራ ማስገባት፤
- ☞ በራሳቸዉ አቅምና ገንዘብ ለመከራከር ለማይችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የነፃ ህግ ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥን ለቀረቡት 100% ማድረስ፤
- ☞ የመሰረተ ማህበረሰብ ፍትህ ለመስጠት ለሚቋቋሙት ባህላዊ ፍርድ ሰጭ አካላት 20% የአቅም ግንባታ ስራ መስራት፤
- ☞ የዜጎች ቻርተር በማዘጋጀት የተገልጋዮችን የእርካታ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት በመፍጠርና በመተግበር የተገልጋዮችን እርካታ 74% ማሳደግ፤
- ☞ በጥናተ ላይ በመመስረት 1 አስተዳደር ፍርድ ቤቶችን / administrative tribunals/ መደገፍ፤
- ☞ የአቤቱታ አቀባበል ውሳኔ አሰጣጥ እና የአቤቱታ ተፈጻሚነት ምጣኔ 99% ማሳደግ፤

**ግብ 4፡- ተቋማት ሙያዊ ነፃነት፣ ገለልተኝነት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፤**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- ☞ ሙያዊና ተቋማዊ ነጻነት/ገለልተኝነት ለማረጋገጥ የሚያስችለ የሕግ ማዕቀፍች፤ የአደረጃጀት እና የአሰራር ስርዓት ለማጠናከር 1 /አንድ/ ህግ እና 1 /አንድ/ ማንዋል ማዘጋጀት፣
- ☞ የወንጀል ምርምራ እና የዓቃቤ ሕግ ዘርፎች ሙያዊ እና ተቋማዊ ነፃነት የሚያረጋግጡ የአደረጃጀት እና አሰራር ስርዓቶችን የሚፈታ 1 /አንድ/ የወንጀል ማስተግበሪያ ማንዋል ማዘጋጀት፣
- ☞ የስነ-ምግባር ጉድለት የታየባቸው ሰራተኞች ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ 100% በዲሲፐሊን ተጠያቂ ማድረግ፤
- ☞ የሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ሲባል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በተመለከተ ለቢሮው አመራርና ሰራተኞች 1 የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና መስጠት፣

**ግብ 5፡- ቅንጅታዊ አሰራር ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- ☞ የመፈጸምና ማስፈጸም አቅምን ለማሳደግ የሚያስችለውን የክልል በፍትህ ዘርፍ ተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር የሚያስችል 4 መድረክ ማካሄድ፤

- ☞ አፈጻጸመን ዉጤታማ ማሳደግ የሚያሰችሉ ባለድርሻና አጋር አካላት ጋር 4 ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር የሚያስችሉ መድረኮችን በባለቤትነት ማካሄድ/መፍጠር፤
- ☞ 1 ጊዜ የፌደራል ፍትህ ሚኒስቴር እና የክልል ፍትህ ቢሮዎች የጋራ የፍትህ ፎረም ዕቅድ፣ ሪፖርት እና ግምገማ ማካሄድ፤

**ግብ 6፡- የህብረተሰቡን ግንዛቤና ተሳትፎ ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- ☞ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ህብረተሰቡን በቅርብ እንድያገለግሉ ለማስቻል ለ12,054 የማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኞች ስልጠና መስጠት፤
- ☞ በሀገር አቀፍ የሽግግር ፍትህ ትግበራ የፍትሕ ቢሮን የስራ ድርሻ 100% ተግባራዊ ማድረግ፤
- ☞ የንቃተ ሕግ ትምህርት የተሰጣቸው ዜጎች ብዛት /ስልጠና ሊሰጠው ከሚገባው ህዝብ /15% ማሳደግ፤

  የንቃተ ሕግ ትምህርት የተሰጣቸው ዜጎች ብዛት /ስልጠና ሊሰጠው ከሚገባው ህዝብ /15% ማሳደግ፤ (ከአብክመ ፕላንና ልማት ቢሮ በተገኘ የአማራ ክልል ጠቅላላ ህዝብ ብዛት የ2019 ትንበያ መሰረት ወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞንን ጨምሮ ወንድ 12,467,000 ሴት 12,585,199 ድምር 25,052,198 ነው፡፡ በዚህም መሰረት የንቃተ ህግ ትምህርት ሊሰጣቸው የሚገቡ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመለየት አረጋውያን ከጠቅላላ ህዝብ 6% ድርሻ፣ አካ/ጉዳተኞች ከጠቅላላ ህዝብ 17% ድርሻ በመውሰድ በበጀት ዓመቱ ጠቅላላ የንቃተ ህግ የሚሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ወንድ 1,795,014 ሴት 1,823,882 ድምር 3,618,897 ነው፡፡) ከዚህ ውስጥ፡-

  - ✓ ህፃናት ወንድ 528,636 ሴት 513,641 ድምር 1,042,277
  - ✓ ወጣቶች ወንድ 562,220 ሴት 582,091 ድምር 1,144,311
  - ✓ ጎልማሶች ወንድ 339,489 ሴት 353,030 ድምር 692,519
  - ✓ አረጋውያን ወንድ 102,569 ሴት 111,949 ድምር 214,518
  - ✓ አካል ጉዳተኞች ወንድ 262,100 ሴት 263,172 ድምር 525,272 በበጀት ዓመቱ ስልጠና የሚያገኙ ይሆናል፡፡
- ☞ የፍትህ ስርዓቱን የሚያጠናክር 1 የህዝብ ምክክር መድረኮች ማካሄድ፤
- ☞ የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን በማጠናከር መረጃዎችን ተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች 100% ለህዝበ ተደራሽነታቸውን ማረጋገጥ፤

- የተቋሙን ስትራቴጂዎች፣ መመሪያዎች እና ዕቅዶች 1 ጊዜ ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ፤
- 1 ዶክመንተሪ ፊልም ማዘጋጀት፤
- ለህብረተሰቡ የህግ ግንዛቤ የሚፈፅሩ የተለያዩ 4 ህትመቶችን በማዘጋጀት ማሰራጨት፤
- ለህብረተሰቡ የህግ ግንዛቤን የሚያሳድጉ እና ለተቋሙ የሚቀርቡ የሚዲያ ጥያቄዎችን 100% ምላሽ መስጠት፤
- የህግ ግንዛቤን የሚያሳድጉ የተመረጠ 1 ተሞክሮ መቀመር፤

**ግብ 7፡- በፍትሐብሄር የፍትህ አስተዳደር የመንግስትና የህዝብ ጥቅሞችን ማስጠበቅ ዉጤታማነት ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ተግባራት፤**

- የክልሉን ህዝብ እና መንግስት ጥቅም በከፍተኛ ሁኔታ የሚጎዱ ጉዳዮችን በመለየት 100% በልዩ ትኩረት መስራት፤
- የመንግስትና የህዝብ መብቶቸና ጥቅሞችን ለማስጠበቅ እንድቻል ለ838 መንግስት መ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- የመንግስትን ሃብትና ንብረት ከብክነት ለመከላከል እንድቻል ለመንግስት ተቋማት የፍትሐብሔር ህግ ምክር አገልግሎት ለቀረቡት 100% መስጠት፤
- በፍትሐብሔር ጉዳዮች የቅድመ መከላከል ስራን ማለትም የዉል ረቂቅ የመመርመር ስራዎችን የቀረቡትን 100% ማከናወን፤
- በፍትሐብሔር ጉዳዮች የቅድመ መከላከል ስራን ማለትም ረቂቅ ዉልን የማዘጋጀት ስራዎችን የቀረቡትን 100% ማከናወን፤
- ጉዳዮች በክርክር ሂደት እንዳይዘገዩና ለበለጠ ወጭ እንዳይዳርጉ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን በድርድር የመፍታት ምጣኔን 23% ማድረስ፤
- በፍትሐብሄር ጉዳዮች በከሳሽና ተከሳሽነት በቀጥታ ክስ፣ በይግባኝ መልስና ሰበር መልስ ክርክሮች የዐቃቤ ህግ መዛግብት የማጥራት/ቅልጥፍና ምጣኔ 99% ማድረስ፤
- ይግባኝና ክስ አያስቀርም የመመርመርና የመወሰን ምጣኔ 100% ማድረስ፤
- የመንግስትና የህዝብ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ በፍትሐብሄር ጉዳዮች የቀጥታ ክስና መልስ የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ ምጣኔን በመዝገብ 92% ማድረስ፤
- በይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የዓቃቤ ህግ የክርክር ውጤታማነት በመዝገብ 70% ማድረስ፤

- በይግባኝና መልስና ሰበር አቤቱታ መልስ መዝገቦች የዓቃቤ ህግ የክርክር ውጤታማነት በመዝገብ 86% ማድረስ፤
- ክስ በቀረበባቸው ጉዳዮች የማስፈጸም አቅምን ለማሳደግ አስቀድሞ ንብረት ፈልጎ የማሳገድ ምጣኔን 65% ማድረስ፤
- የተወሰደን የመንግስትና የህዝብ ሃብት ተመላሽነት ለማሳደግ የአፈጻጸም ክስ ከቀረበባቸው ጉዳዮች ውስጥ የማስፈጸም አቅም በመዝገብ 98% ማድረስ፤

**ግብ 8፡- የህግ አገልግሎት አሰጣጥ ዉጤታማነትን ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ተግባራት፤**

- የሙያና ሲቪክ ማህበራት በፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ የሚሳተፉበትን ሁኔታ መንደፍና 1 ጊዜ መተግበር፤
- ለ10 የመንግስት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች ነገረ ፈጀችን የህግ ገልግሎት  አሰጣጥ ክትትል ማድረግ፤
- የሌሎች የመንግስት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች ነገረ ፈጀችን አምስት /1/ ጊዜ ስልጠና መስጠት፤
